Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# የኮቪድ/COVID-19 ክትባት AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ

ወቅታዊ የሆነበት ቀን: 30 ሐምሌ/July 2021 ዓ.ም

## ስለ ክትባቱ

ዛሬ የ**AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት** አግንተዋል።

ይህ ክትባት የሚከላከለው በAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ለሚፈጠር ህመም ማንኛውንም ህይወት ያለው SARS-CoV-2 ቫይረስን አያካትትም (ለኮቪድ/COVID-19 ምክንያት ለሚሆን ቫይረስ)፤ እንዲሁም ይህ ለርስዎ ኮቪድ/COVID-19 አጋልጦ መስጠት አይችልም። ስፓይክ ፕሮቲን/spike protein ለተባለ የSARS-CoV-2 ቫይረስ ጠቃሚ የሆነ አካል የጀነቲክ ኮድ ዝርያን ያካተተ ነው። የስፓይክ ፕሮቲን በመደበኛ ጉንፋን "ተሸካሚ" ቫይረስ (የአደኖቫይረስ/ adenovirus) ላይ እንደገባ ነው። የአደኖቫይረስ ተሸካሚ በሰውነትዎ ሴሎች/ህዋስ ላይ ስፓይክ ፕሮቲን ስለሚያመጣ፤ መጀመሪያ ስለ ስፓይክ ፕሮቲን ማንበብ መቻል እንዳለባቸውና ቅጂውን ማግኘት ይኖርባቸዋል። ከዚያም የርስዎ በሽታ መቋቋም ሀይል አሰራር ቫይረሱን በመገንዘብ ከSARS-CoV-2 ቫይረስ ጋር ይዋጋል። የአደኖቫይረስ ተሻሽሎ ስለተለወጠ አንዴ በሴሎች/ህዋስ ውስጥ ከሆነ ሊባዛ አይችልም። ይህ ማለት ወደ ሌሎች ህዋስ እንደማይሰራጭና ብክለትን መፍጠር እንደማይችል ነው።

## ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ምን እንደሚጠበቅ

እንደ ማንኛውም ክትባት የኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ አንዳንድ ችግሮች ሊፈጠር ይችል ይሆናል።

**የAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት** ከወሰዱ በኋላ ከሚፈጠሩ **የተለመደ** ችግሮች:

- መርፌውን በተወጉበት ቦታ ህመም፤ እብጠት፤ የመቅላት ወይም ማሳከክ
- የድካም መንፈስ
- እራስ ምታት
- የጅማት ህመም
- ማቅለሽለሽ
- ትኩሳትና ብርድ ብርድ ማለት
- ደህና አለመሆን ስሜት
- የመገናኛ ህመም ይሆናል።

**AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት** ከወሰዱ በኋላ ከሚፈጠሩ ባልተለመደ ቀላል ችግሮች ላይ የሚካተት:

- በመገጣጠሚያ ያለ ትልቅ የፈሳሽ እብጠት
- በእጅ እግር ላይ ህመም
- ግራ መጋባት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ

- የሆድ እቃ ህመም ይሆናል።

እነዚህ የሚከሰቱት ችግሮች ብዙጊዜ መካከለኛ ናቸው። እነዚህ የሚከሰቱት ክትባቱን ለወሰዱ በሁለት-ዕስተኛ ሰዎች ሲሆን የሚጀምረውም ክትባቱን በወሰዱበት ቀን እንደሆነና በአንድ ወይም በሁለት ቀናት ይጠፋል።

በአንዳንድ ሰዎች ላይ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከሌሎች ክትባቶች ጋር ሲነጻጸር በበለጠ እንደ ኢንፍሎዌንዛ/ፍሉ የመሰለ ምልክት እንደሚፈጥሩ፤ ይህም እስኪጠፋ ድረስ ጥቂት ጊዜ ሊወስድ ይችላል። እነዚህ የህማም ምልክቶች የሚፈጠሩት ከሁለተኛ መጠን እቅን ክትባት ጋር ሲወዳደር ክስተቱ በጣም የተለመደው በመጀመሪያ መጠን ክትባት ይሆናል።

መርፌ በተወጉበት ቦታ ላይ ካመመዎት ወይም ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ በመጀመሪያ ከ1–2 ቀናት ትኩሳት፤ እራስ ምታት ወይም ሰውነት ማሳከክ ካለብዎት ፓራሰቲሞል/paracetamol የህመም ማስታገሻ መውሰድ ይችላሉ። ይህ ከዚህ በላይ ላሉት ምልክቶች እንዲቀንስ ይረዳሉ። ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ፓራሰቲሞል/paracetamol ወይም ኢቡፕሮፊን/ibuprofen መውሰድ የለብዎም። መርፌውን በተወጉበት ቦታ እብጠት ካለ የቀዝቃዛ ጨርቅ ማሰሪያን መጠቀም ይችላሉ።

**AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት** ከወሰዱ በኋላ **አልፎ አልፎ** ለተከሰቱ ችግሮች የተደረገ ሪፖርት:

- የአለርጂ መከሰት (አለመስማማት/anaphylaxis)፡
  - የAstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከወሰዱ በኋል የሚፈጠር አለመስማማት/ Anaphylaxis በጣም አነስተኛ ነው። በአውስትራሊያ ውስጥ የሚታየው መጠን ከሌሎች ክትባቶች ጋር ተመሳሳይ ይመስላል።
- ትሮምብፕሲስ ከትሮምቦችይቶፕኒያ በሽታ ምልክት/(TTS) የተባለ ሁኔታ ላለበት የደም መርጋት (thrombosis) እና አነስተኛ ፕላተለት/platelet ደረጃ (thrombocytopenia) ሊከሰት ይችላል:
  - ከአውስትራሊያና ውጭ አገራት መረጃ የሚያሳየው ለTTS የመከሰት ቁጥር አነስተኛ መጠን እንደሆነ ነው
  - የደም መርጋር በተለያየ ሰውነት አካል ሊፈጠር ሲችል፤ ይህም አንጎልን ያካትታል (ይህ የሰረብራል ቨኑስ ሳይነስ ትሮሞሲስ/cerebral venous sinus thrombosis) እና የአብዶመን/abdomen ሲባል (ይህ idiopathic splanchnic vein thrombosis ተብል ይጠራል)። አነስተኛ የደም ፕላተለት ቁጥር/platelet ለመድማት ምክንያት ሊሆን ይችላል።
  - የዚህ ሁኔታ በሽታ ምልክት የሚፈጠረው ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከ4 እስከ 42 ቀናት ባለው ጊዜ ነው።
  - የዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለባቸው ሰዎች በጣም ስለሚያማቸው ወደ ሆስፒታል መሄድ አለባቸው። ይህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ የአካል ጉድለት እና ለሞትም ሊያዳርግ ይችላል።
  - ስለ TTS የበለጠ መረጃን ማግኘት የሚቻለው በታካሚ የመረጃ ጽሁፍ ወረቀት/Patient information sheet በAstraZeneca COVID-19 vaccine እና በ TTS ላይ ማግኘት ይቻላል።

**ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከዚህ በታች ያሉት ካለብዎት ህክምና ማግኘት አለብዎት:**

- የአለርጂ አለመስማማት ችግር አለብኝ ብለው ካሰቡ። ከባድ ችግር ካጋጠምዎት እንደ የመተንፈስ ችግር፤ ከትንፋሽ እጥረት ድምጽ፤ ፈጣን የልብ ትርታ ወይም እራስን የመሳት ችግር ካጋጠምዎት በ 000 መደወል።
- ክትባቱ ከወሰዱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሊጠፋ ባልቻለ የተከሰተ ችግር ካጋጠምዎት ይሆናል።
- በተለይ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከ4 እስከ 48 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ከዚህ በታች ያሉት የበሽታ ካለብዎት:
  - ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ከ48 ሰዓታት በላይ ወይም ከ48 ሰዓታት በኋላ ከባድ የማይጠፋ እራስ ምታት ካለብዎት ነው። በመጀመሪያ ቀላል የህመም ማስታገሻው የራስ ምታቱን ሊያባብሰው ይችል ይሆናል ነገር ግን ይረጋጋል
  - የብዥታ እይታ
  - የክንድና የፊት መዳከም
  - መደናገር ወይ የአእምሮ መሳት/seizure።
  - የትንፋሽ እጥረት
  - የደረት/ሳንባ ህመም
  - የማያቋርጥ የሆድ እቃ ህመም
  - የእግር ማበጥ
  - ብክለት ባለበት ቦታ ላይ ሳይሆን የሽፍታ ወይም ጠባሳ ለመግለጽ የማይቻል ችግር ካለ ነው።

በቅርቡ ክትባቱን እንደወሰዱ ለሀኪምዎ ማሳወቅ ማረጋገጥ። አስቸኳይ ላልሆነ የበሽታ ምልክቶች ለመደበኛ የጤና ጥበቃ አቅራቢዎ (ለርስዎ አጠቃላይ ሀኪም/GP) ማየት ይችላሉ።

## ለክትባት ደህንነት መቅከታተል እና ለሚከሰት ችግር ሪፖርት ስለማድረግ

ለሚከሰት የተጠረጠሩ ችግሮች ለርስዎ የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ወይም ለሌላ የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። ከዚያም እርስዎን በመወከል መደበኛ የሆነ ሪፖርት ለርስዎ አስተዳደር ግዛት ወይም ተሪቶርይ የጤና መምሪያ ቢሮ ወይም በቀጥታ ለህክምና ጥራት አስተዳደር (TGA) ያቀርባሉ።

ይህንን በራስዎ ሪፖርት ለማድረግ ከፈለጉ፤ እባክዎ ለTGA በድረገጽ: https://www.tga.gov.au/reporting-suspected-side-effects-associated-covid-19-vaccine ላይ ማየትና በገጹ ላይ ያለን መመሪያ መከተል።

## ክትባት ከወሰዱ በኋላ የኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ስለማካሄድ

ከኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰድ ጋር ከሚፈጠሩት አንዳንድ ችግሮች ከኮቪድ/ COVID-19 ምልክቶች (ለምሳሌ፡ ትኩሳት) ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ለማንኛውም ህይወት ላለው የ SARS-CoV-2 ቫይረስ እንደማያካትትና ለርስዎ በኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ ማጋለጥ እንደማይችል ነው። ለኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድ ወይም ከሌላ ሰው መገለል ላያስፈልግዎት ይችላል:

- ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ በመጀመሪያ ሁለት ቀናት ውስጥ አጠቃላይ የሆነ የበሽታ ምልክቶች እንደ ትኩሳት፤ የራስ ምታት ወይም የድካም መንፈስ ካለብዎት፤ <u>እና</u>
- ምንም ዓይነት የትንፋሽ ችግሮች መኖር እርግጠኛ ካልሆኑ (ለምሳሌ፡ በአፍንጫ ፈሳሽ ፤ መሳል፤ የጉሮሮ ህመም፤ የትንፋሽ ወይም የጣዕም ስሜት ማጣት) ከሌለብዎት ነው።

ይሁን እንጂ በርስዎ አስተዳደር ግዛት/ተሪቶርይ ላለው ወቅታዊ መመሪያዎች የተሰጡትን የቅርብ ጊዜ መረጃ ማጣራት አለብዎት። በርስዎ አካባቢዎች ውስጥ በሚካሄድ ድርጊት ላይ ለሚከሰት የኮቪድ/COVID-19 ወረርሽኝ በዚህ ምክር ሊቀይረው ይችላል። ሌሎችን ቅድመ ሁኔታዎች ቢያሟሉም አሁንም የኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድ ሊኖርብዎት ይችላል። ለምሳሌ፡ በታወቀ የኮቪድ/ COVID-19 ካለበት በቅርበት ግንኙነት ካደረጉ ነው። ጥርጣሬ ካለብዎት የህክምና ምርመራ ያስፈልጋል።

## ለሁለተኛው ቀጠሮዎ ማስታወስ

በ12 ሳምንታት ልዩነት ያለዎትን የሁለተኛ ጊዜ መጠን/doses AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መውሰዱ አስፈላጊ ነው። በክትባት መጠን/ doses መካከል ያለውን ልዩነት ከ12 ሳምንታት ወደ 4 ሳምንታት በታች ያለውን ልዩነቱን በመቀነስ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ትክክለኛ ሊሆን ይችላል። የሁለተኛ ጊዜ መጠን/dose ክትባት ከኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ በተሻለ መከላከያ ዘዴ ሊሆን ይችላል።

## በርስዎ ቀጠሮ ላይ ያቀረቡት መረጃ እንዴት ይጠቅማል

እንዴት ስለርስዎ ግላዊ ዝርዝር መረጃ እንደሚወሰድ፤ እንደሚቀመጥ እና መጠቀም እንደሚቻል መረጃ በድረገጽ https://www.health.gov.au/using-our-websites/privacy/privacy-notice-for-covid-19-vaccinations ላይ ገብቶ ማየት።